# ከ እስራኤል አምላክ የተወሰዱ ስንኞች

*ያያት ቅድም አያቶቻችን ጀግንነት፣*
*መሰረቱ፣ የነፃነታቸው፣*
*ጦር አወራወራቸው፣ ብቻ አልነበረም፣*
*ጋሻ አመካከታቸው፤*
*ያላረሱትን አለመብላታቸው እንጅ፣*
*ያልፈተሉትን አለመልበሳቸው፡፡*

# ትፍ ትፍ አትደጉ

ፊታቸው ጨምዳዳ፣ ቅርፀ ቢስ ሽምድምዶች፣
ከመሆን አልፈው ያድጋሉ፤ ልጆች፣ የሰው ልጆች፡፡
ውትር ውትር ብለው፣ ተራምደው፣
ይስቃሉ ተፍለቅልቀው፤ ያወራሉ ተኮላትፈው፣
ካንደበታቸው ቃል ወጥቶ፤ ጣፋጩ፣
ከልቦናቸው ሀሳብ ፈልቆ፣ ንፁሁ፣
ይናገራሉ፡፡

አደጉ ይባላል ከዚያማ፤ ተለቁ፣
ንፁህ ልባቸው ሲደፈርስ፣ ሰው መሆናቸውን ሲያውቁ፡፡

ልጅ ሆነው ቢቀሩ ሁሌ፣ መተለቁ ቢቀር ምናለ፣
ልቦናቸው እንደጠራ፣ አፋቸው እንደጣፈጠ፣
ምናለ ባያውቁ፣ ባያድጉ፣
ልባቸውን መሸጥ፣ ፍቅራቸውን መግዛት ባይለምዱ፤
ምናለ…

---

አምሀ አስፋው፡፡11/09/99
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፡፡

# ምስጋና

ረስቼዋለሁ ስሙን፣
የመደብሩን፤
ረስቼዋለሁ፡፡

ግን ከቸርቸል ጎዳና፣ ካንገቱ ላይ ከጠባቡ፣
የመፅሀፍት መደብር ነበር፣ የማልረሳው በቀላሉ፡፡
ተቀርፀዋልና በልቤ፣
መፅሀፍቱ፣
ባለቤቱ፣
ደግነቱ፡፡

አስር ብር ይገኔ፣ የተረፈች ከሲኒማ፣
የተረፈች ከበቅለባ፣
እገባለሁ ከዚያች ሱቅ፣
መፅሀፎች ልገዛ፡፡
እጣውላው ላይ ተቀምጬ፣
ከምድር ጥግ ካለው መደርደሪያ፣
የምወዳቸውን መፅሀፎች መርጬ፣
አስር አስራምስቱን ይገኔ እቀርባለሁ፣
ብር እንዳለው ቱጃር ተኩራርቼ፡፡

ያይና ባለቤቱ፣
«ሳይሸጡ የቆዩ መፅሀፎች ናቸው፣
ልባሳቸው የሻገተ፣
ዛሬ አንተ ባትገዛቸው፣
ነገ እኮ መጥ-ጣያቸው ነበረ፡፡
ስለዚህ አስር ብር አምጣና፣
ውሰዳቸው በሙሉ፣»
ብሎ ያሰናብተኛል፣
አሸክሞኝ ያን ሁሉ፡፡

አይገባኝም ነበር ግን፣
ግዥዬ መሆኑ ስጦታ፣
ማንበብ ለሚፈልግ ትንሽ ልጅ፣
ደግ ሰው ያረገው ችሮታ፡፡

ዘመኑ ሩቅ ቢሆንም፣
ባለቤቱንም ባላውቀው፣
ለሰውም ለዘመኑም፣
እግዜር ይስጥልኝ እላለሁ፤
ዘመኑ የተስፋ ነበርና፣
ፍቅር የሰፈነበት፣
ሁሉ በገንዘብ የማይሸጥ፣
ገንዘብ ሁሉን 'ማይገዛበት፤

ስለዚህ እግዜር ይስጥልኝ እላለሁ፣
ምን አደርጋለሁ ሌላ፣
አሁንም አስር ብር ነው ያለኝ፣
የተረፈኝ ከቡና፡፡

---

አምሀ አስፋው፡፡ ኒው ኦርሌንስ፣ ሉዚያና፡፡ 11/25/99 እአ፡፡

# ወሊሶ

አሶች፣
ከሜክሲኮ ባህረ-ሰላጤ፣ ተነስተው፤
የሚሲሲፒን ወንዝ ወደላይ ዋኝተው፤ አቋዋርጠው፤
ይደርሳሉ ከተወለዱበት፤ ከቀዬአቸው፣
ለሌላ አይደለም ለመሞት፣
ራሳቸውን ለመመለስ፤ ከህይወት ወደምንምነት።

አፈር ነህና፣ ትመለሳለህ ይላል ወዳፈር፣ መጣፉ፤
የትኛውን ይሆን ማለቱ፣
ብዙ ነውና አፈር አይነቱ፣ ብዙ።

ከደጅ ዝናብ ዘንቦ፣
ሲወጣ ፀሀይ ያም አባርቶ፣
ያፈሩ ጠረን ሲተን፣ ከምድር ማህፀን ተነስቶ፤

ከቤት፤ አንተም ስትተን፣ የናትህን ማህፀን ለቀህ ገና፣
የመጀመሪያህን አየር ስትተነፍስ፣ በመሀል ትገናኙና፣
ትዋሀዳላችሁ ለዘለአለም፣
አንተና፣ የተወለድክበት ቤት አፈር።

ለምን ይናፍቀኛል፣ እንዲያ ካልሆነ ሚስጥሩ፣
አላንድ ቀን አላየሁት፣ ለነገሩ፣
ለምን ይናፍቀኛል፤ አለዚያ፣
ወሊሶ።

---

አምሀ አስፋው
2/12/1999 አእ
ኮሎምቢያ ሚዙሪ

# ፋጡማ

አላየሁዋትም ዘንድሮ፣ ብዙ፣
ሲነፍስ፣ ሲናፈስ ሰምቼ ነበርና፣ እንዳዘነበለ ሚዛኑ፣
እንዳልሆነ ለፋጡማ፣ የሲድኒ ውሀው ጠበሉ።
ሲበር ነበር ወሬው፣
አንሰራፍቶ፣
ሲበር ነበር።

ትወጣ ይሆናል ከወርቅ ቡድን፣ ድል ካረጉት በሲድኒ፣
        ሮጣ፣ አሸንፋ፣ እንድሮው ሁሉ አብርታ፣
አላይዋትምና ወገኖችዋ፣
አላየቻትምና አገርዋ፣ ኢትዮጵያ።

እዚህ ግን፣ ተቀርፃለች ባትላንታ፣
ዳግመኛ በወርቅ ላትመዘን፣ ልቤን ጥላ ላትወጣ።
በንዲራዋን ስትስም አይቼ፣ ያነደድኩት እሳት ከውስጤ፣
ቀርፅዋታልና ለዘላለም፣ ወይም ለቀረችኝ ትንሽ እድሜ፣
ወርቅ ከማይገባበት ንፁህ ቦታ፣ ገንዘብ ከማይደርስበት ልቤ።

ድል አድራጊ ናት ሁሌ፣
ድል አድራጊ ናት ለኔ፣
ድልአድራጊ ናት ለዘላለም፣
ፋጡማ።

---

አምሀ አስፋው
10/11/00 ኢ.እ
ኮሎምቢያ፣ ሚዙሪ

# አባት ካለህ እሩጥ

ሆዴን ቢያመኝ፣
ልቤ በፍጥነት ቢመታ፣
ቢዘል ቢፍጨረጨር፣
ቢመስለኝ ደረቴን ስቶ ሊወጣ፣
አልጨነቅም ነበር ብዙ፣
እንደሚያድነኝ ስለማውቅ፣ አባቴ፣
ካለ ከቤት ካጠገቤ፡፡

አሁን ግን ሞተ፣ አፈር በላው፣
እናቴም አልቀረች፣
    አብራው ሄደች ተከትላው፣

ማን ይሆን ከእንግዴህ፣ የሚያድነኝ፣
ሲያመኝ?

ማንን አምኜ ይሆን፣
    የክፍሌን መብራት የማጠፋ፣
ጨለማውን የምደፍር፣
    መናፍስቱን የማልፈራ፡፡

---

አምሀ አስፋው
10/18/00 አ.እ
ኮሎምቢያ፣ ሚዙሪ

# አጠራጠረኝ

ትዝ ይለኛል አንዴ፣
መፃፌ፣
የረገፈ ዛፍ ቅጠሉ፣
እንደሚያለመልም እንደገና፣ ሲያልፍለት ብሩዱ፣ ክረምቱ፡፡
አጠራጠረኝ ግን አሁን፤ ዛፉ፤
ማቆጥቆጡ፣ ማበቡ፣
ቁሩ፣ ዝናቡ፣ ማብቃቱ፣
ይሄ ክረምት መውጣቱ፣
አጠራጠረኝ፡፡

---

አምሀ አስፋው
6/10/2000 አእ
ኮሎምቢያ ሚዙሪ

# የሚዞ ነብር

የክረምቱ መባቻ ላይ፣ ቁሩ ብርዱ ሲጀምር፣
ከነሀስ የተሰራ፣ የወርቅና የጥቁር ዥንጉርጉር፣
ነብር፣
ያካባቢው ባለስልጣን ተሰብስቦ፣
ተማሪው ሙዚቀኛው፣ ጥሩንባውን ነፍቶ፣ ጨፍሮ፣
አቆመው ካደባባይ፣ እንዲታይ በአንክሮ።

እኔም አየዋለሁ፣ በቀን ሶስቴ አራቴ፣
በወጣሁ በገባሁ ቁጥር፣ ከስራየ ከቤቴ።

ሲደክመው አይጋደም፣ እንደትውልድ ሀገሩ፣
ሲበርደው አይጠጋ፣ ከዘመድ ከአዝማዱ፣
ሲሞቀው ጥላ አይሻ፣ አይደበቅ ከሀሩሩ፣
«አይ ስቃዩ» አልኩ በልቤ፣ «አየ ፍዳው፣ አይ ችግሩ።»

ይታዩት ይሆን ዘመዶቹ፣ በኩራት ሲራመዱ፣
ወርካው ስር ሲተኙ፣ ግራሩን ሲታከኩ፣
ሲርባቸው ሲጠማቸው፣ የነገ ምግባቸውን ሲፈልጉ።
ይሰማዋል መሆኑ፣ አለመራብ በድንነት፣
ያለህይወት የቆመ፣ የድንጋይ ጥርብ የናስ ብረት፤
ይሰማዋል!

ብየ ሳዝን፣
ለናስ ነብር፣
ድንገት ታየኝ፣ ሚስጥሩ፣
የኔም ህይወት፣ ያው መሆኑ፣
ድንገት ታየኝ።

---

አምሀ አስፋው
ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፭ አም (11/05/02 አእ)
ኮሎምብያ፣ ሚዙሪ

# መች አወቀች (ለቪነስ ዊሊያምስ)

አቀንቃኞቹ፣
ጆን ማክንሮና፣ ክሪስ ኤቨርት ነበሩ።
አሜሪካኖች ናቸው፣ ለነገሩ፣
ቪነስም እንዲሁ፣
መስልዋት ነበር፣ የምትፋለም ከቤልጅግ፣
        የምትጫወት ከሜዳ፣
                ከዊምብልደን ሜዳ፣
አገር ወገንዋን ወክላ፣
አገር ወገንዋን ተመስላ።

ሳምንቱን በሙሉ፣ የነበረው ሲወራ፣
ጄነፈር፣ ከሊንዚ ጋር ተጋጥማ፣
ያቺም አሸነፈች፣ ያች፣
        ይሆናል ተብሎ ነበር፣ ድሉ፣
                ያሜሪካ፣
የነጭ አሜሪካ።

ቀረ ምኞትዋ፣ የኤቨርት፣ ሳይሳካ፣
ተደመሰሰች፣ ዳቨንፖርት፣
        ፈረካከሰች፣ ካፕሪያቲ፣
                የነጭ ዘር ተስፋ፣ ያሜሪካ።

ማክንሮ፣ አፍ አውጥቶ፣
ምን አፍ ብቻ፣ አይን አውጥቶ፣
ሄነን ታሸንፋለች አለ፣
        ቪነስ፣ ያገሩ ሰው መሆንዋን ረስቶ።

የነጭ አለም የቆመበት፣ መሰረቱ፣
ዘር እንጅ፣ ብሄር እንዳልሆነ እውነቱ፣
መች አወቀች፣ ቪነስ፣
        የዘርዋ እንጅ፣ ያገርዋ ሰው እንዳልሆነች።

መች አወቀች፣ ቪነስ፣ እንዳዬ ቴወድሮስ ሁሉ፣
የነጮች እውነት የሚፈልቅበት፣ የሚቀዳበት ምንጩ፣
ማተባቸው እንዳልሆነ፣ የፍቅራቸው ማእዘኑ፣
መች አወቀች።

---

ሀምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፫ አም (7/8/2001)

ውጤት፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቪነስ | 6 | 3 | 6 |
| ሄነን | 1 | 6 | 0 |

# አትፍረዱ

«ዩ» የተባለውን መንገድ ስትቃኙ፣ ያበሻን መርመስመሻ፣
ቀና ብላችሁ ተመልከቱ፣ በጥሞና፣
ሌላም መንገድ እንዳለ፣ ጠባብ የህይወት ጎዳና፡፡
ለመውጣት የሚያስቸግር፣ አንዴ ከገቡ በሁዋላ፣
ግራ ቀኙ የጨለመ፣ ግራ ቀኙ የተዘጋ፣
አበሻ የሚመላለስበት፣ ሌላ የህይወት ጎዳና፣
ተመልከቱ እንዳለ፣
ተመልከቱ፡፡

እንዲያ ስትመለከቱ፣ ቶላን ካያችሁት ተክዞ፣
የሚጠጣው አጥቶ፣ ተጠምቶ፣
ወይ የሚብ-በላ ቸግሮት፣ ተርቦ፣
አትፍረዱ፡፡
«ለምን እንዲህ ሆነ?» አትበሉ፣ መፍረድ ነውና ማለት እንዲያ፣
አትፍረዱ ይል የለ፣ መፅሀፉ፣ ይፈረድባችሁዋልና፣
ስለዚህ አትፍረዱ፡፡

አናውቅም፣ ምን እንዳረገዘ፣
ነገ፡፡
መንገዱ፣ መመላለሻችን፣
የትኛው «ዩ» እንደሚሆን፣ መዋያ፣ ማደሪያችን፣
አናውቅም፡፡

ስለዚህ አንፍረድ፣ የመፅሀፉን ምክር እንስማ፣
ስላልሆነ ንብረታችን፣ ነገን አናውቀውምና፡፡

---

አምሀ አስፋው
መጋቢት 26 ቀን 1995 አ.ም
ኮሎምቢያ፣ ሚዙሪ